# የኢትዮጵያ የምግብ፣ መድኃኒትና ጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለስልጣን

## በፕሮጀክት ሥራ የላቦራቶሪ የጥራት ምርመራ የሰራተኛ የክፍያ መመሪያ 388/2013

መስከረም /2009

አዲስ አበባ

# መግቢያ

የኢትዮጵያ የምግብ፣ መድኃኒትና ጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለስልጣን የላቦራቶሪ ጥራት ፍተሻን ከቅድመ ገበያ ይልቅ ለኮንሳይንመንት እና ድህረ ገበያ ትኩረት በመስጠቱና የድህረ ገበያ ጥራት ምርመራ ስራዎች የፕሮጀክት ባህሪ ያላቸው በመሆኑ፤

የድህረገበያ ጥራት ምርመራን በስፋት ለማከናወን የስራው ባህሪ ባለሙያዎች እና ሌሎች ሰራተኞች ከመደበኛ የመንግስት የስራ ሰዓት ውጪ ተግባራትን እንዲያከናውኑ የሚፈልግ በመሆኑ፤

ለላቦራቶሪ ጥራት ምርመራ የሚያስፈልጉ የተለያዩ ወጪዎችን ለመሸፈን እና የላቦራቶሪውን አለም አቀፍ እውቅና ለማስቀጠል የገንዘብ አቅም የሚያስፈልግ በመሆኑ፤

አስፈላጊውን የጥራት ምርመራ በወቅቱ እና በጥራት በማከናወን ለቁጥጥር ግብዐት እና ለተለያዩ ዓላማዎች የሚረዳ የላቦራቶሪ ጥራት ምርመራ ውጤቶችን በዜጎች ቻርተር በተቀመጠው ወይም በአጭር ጊዜ ማውጣት አስፈላጊ በመሆኑ፤

በአጠቃላይ ግልጽነት እና ተጠያቂነት ያለው የአሰራር ስርአት ማስፈን አሰፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ በአጋር አካላት ድጋፍ እና በተለያዩ ፕሮጀክቶች መልክ የላቦራቶሪ ጥራት ምርመራ በሚሰራበት በማንኛውም ወቅት የሚሰበሰብን የአገልግሎት ክፍያን የአጠቃቀምን ሁኔታና ሌሎች ተያያዥ ጉዳዮችን በተመለከተ ይህ መመሪያ ወጥቶአል፡፡

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ

## 1. አጭር ርዕስ

ይህ መመርያ "የላቦራቶሪ የጥራት ምርመራ የክፍያ እና የማትግያ ስርዓት መመሪያ ቁጥር 388/2013 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

## 2. ትርጓሜ

የቃሉ አግባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ ፡-

1)“ላቦራቶሪ” ማለት የምግብ፣ የመድኃኒት እና የህክምና መገልገያ መሳርያዎች የጥራት ፍተሻ የሚደረግበት የባለስልጣኑ የዋናው እና የቅርንጫፍ ጽ/ቤት ላቦራቶሪ ነው፡፡

2) “ባለሙያ” ማለት በጥራት ምርመራ ላይ ተሳትፎ ያደረገ ልምዱ፣ ክህሎቱ እና እውቀቱ ያለው በባለስልጣኑ የተለያዩ የስራ ክፍል የሚሰራ ሰራተኛ ነው፡፡

3) “አመራሮች” ማለት በጥራት ምርመራው እና ተያያዥ ተግባራት ላይ ተሳትፎ ያደረጉ በባለስልጣኑ በተለያዩ የስራ ክፍሎች ያሉ መካከለኛ አመራሮች ናቸው፡፡

4) “የላቦራቶሪ ጥራት ምርመራ ውጤት ገምጋሚ” ማለት የላቦራቶሪ ጥራት ምርመራ ውጤት ግምገማ ላይ ተሳትፎ እንዲያደርጉ በላቦራቶሪ ኳሊቲ ማንዋል መሰረት ዳይሬክቶሬቱ የለያቸው ልምድ ያላቸው የላቦራቶሪ ባለሙያዎች፣ ቡድን አስተባባሪዎች እና አመራሮች ናቸው፡፡

5) “ድጋፍ ሰጪ ሰረተኞች ” ማለት በፋይናንስ፣ ግዢ እና የጠቅላላ አገልግሎት ስራ ላይ የተሰማሩና በአጋር ድርጅቶች ድጋፍ እና በፕሮጀክት ለሚሰሩ ስራዎች የሚውሉ ግብዐቶች ግዢንና መሰል ተግባራትን ከመደበኛ የስራ ሰኣት ውጪ ስራው ላይ የተሳተፉ ሰራተኞች እና አመራሮች ናቸው፡፡

6) “ከአጋር አካላት ጋር የሚሰራ ስራ” ማለት ከባለስልጣኑ ጋር በውል ስምምነት የተያዘ፣ ለስራው የሚስፈልገው በጀት የተመደበለት፣በጊዜ ገደብ የተወሰነ ማንኛውም በጋራ የሚከናወን የቁጥጥር ስራ ሆኖ በመደበኛ ወይም ከመደበኛ የስራ ሰዓት ውጪ ሊከናወን የሚችል ተግባር ነው፡፡

7) “ፕሮጀክት” ማለት ለተለያዩ ሀገራት፣ድርጅቶች፣ግለሰቦች፣አምራቾች እና ሌሎች አካላት ጥቅም ላይ ሊውል የሚችል የጥራት ምርመራ ስራ ሲሆን በውል በተያያዘ ሰነድ መሰረት ለአንድ ወይም ከአንድ ጊዜ በላይ ሊያገለግል የሚችል ሆኖ ባለሙያዎች ከመደበኛ የመንግስት የስራ ሰዓት ውጪ ተግባራትን በማከናወን የሚፈጸም ነው፡፡

8) “የምርመራ ስራ አጣሪ ኮሚቴ” ማለት ከምርመራ ስራ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን የክፍያ፣ የስራ ምደባ፣ አስተዳደራዊ እርምጃ እና ሌሎች ጉዳችን አስመልክቶ የሚቀርቡ ቅሬታዎችን ወይም አለመግባባቶችን ተቀብሎ የሚመለከት ከተለያዩ ዳይሬክቶረተቶች እና የስራ ክፍሎች የተውጣጣ አካል ነው

9) “መደበኛ ስራ” ማለት በመንግስት የስራ ሰዓት የባለስልጣኑን ተልዕኮ ለማሳካት የሚከናወንና በቅርብ ሀላፊ እውቅና ያለው ማንኛውም ተግባር ሲሆን ከ ሰኞ እስከ ሀሙስ ከ 2፡30 እስከ

6፡30 እና ከ 7፡30 እስከ 11፡30፤ እርብ ከ 2፡ 30 እስከ 5፡ 30 እና ከ 7፡ 30 እስከ 11፡ 30 ባለው የስራ ሰዓት የሚከናወን ነው፡፡

10) "የአሰራር ስርአት" ማለት ማናኛውም በመንግስት ወይም በባለስልጣኑ ለአሰራር ግልፅነት፤ቀልጣፋነት ወይም ተጠያቂነት ሲባል በስራ ላይ የሚውል ሰነድ ነው

11) "ባለስልጣን" ማለት የኢትዮጵያ የምግብ፤ የመድኃኒትና የጤና ክብካቤ አስተዳደር እና ቁጥጥር ባለስልጣን ነው፡፡

12) "አዋጅ" ማለት የኢትዮጵያ የምግብ፤ የመድኃኒትና የጤና ክብካቤ አስተዳደር እና ቁጥጥር አዋጅ 661/2002 ነው፡፡

13) "ሰው" ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፡፡

14) ማንኛውም በወንድ ጾታ የተገለጸው ሴትንም ይጨምራል፡፡

## 3. ዓላማ

*የዚህ መመሪያ ዓላማ፡-*

1) የባለስልጣኑ ባለሙያዎች እና ሰራተኞች በአጋር አካላት ድጋፍ እና በፕሮጀክት ስራዎች ላይ በትርፍ ሰዓት፣ በበዓላት እና ከስራ ሰዓት ውጪ ለሚሰሯቸው የላቦራቶሪ ጥራት ምርመራ እና ተያያዥ ተግባራት የማትግያ ክፍያ ስርዓት ለመዘርጋት፤
2) በጥራት ምርመራ ወቅት ባለስልጣኑ ለሚያወጣቸው የተለያዩ ወጪዎች ከተለያዩ አጋር አካላት ለሚገኝ ድጋፍ ዝርዝር የወጪ ስሌት ስርአት ለመዘርጋት፤
3) የላቦራቶሪውን አለም አቀፍ እውቅናን ወሰንን ለማስፋት እና ቀጣይነቱን ለማረጋገጥ የሚያስችለውን የላቦራቶሪውን የገንዘብ አቅም እና የሰው ሀይል በባለሙያ ስብጥርም ሆነ በብዛት ለማሳደግ ፤

## 4. የተፈጻሚነት ወሰን

1) ይህ መመርያ  በተለያዩ አጋር አካላት እና ፕሮጀክቶች ድጋፍ በሚከናወን ማንኛውም የላቦራቶሪ ጥራት ምርመራ ተግባር ላይ ተፈጻሚነት ይኖረዋል፡፡
2) ከአጋር ድርጅቶች እና ፕሮጀክቶች ድጋፍ ውጪ የሚገኝ የጥራት ምርመራ አገልግሎት ክፍያ እና አጠቃቀም በዚህ መመርያ የሚስተናገድ አይሆንም፡፡

3) በዚህ ስራ ላይ የሚሳተፉ ባለሙያዎች ከኬሚካል ጋር በተያያዘ ሊደርስ የሚችሉ ጉዳቶች ማካካሻ እና ከምርመራ ስራው ጋር ተያያዥ ባለሆኑ አስተዳደራዊ ጉዳዮች ላይ የሚነሱ ቅሬታዎች  በዚህ መመሪያ የሚስተናገዱ አይሆንም፡፡

## ክፍል ሁለት
## የጥራት ምርመራ አይነቶች

### 5. ስለ ላቦራቶሪ ጥራት ምርመራ አገልግሎት ዓይነቶች

1) በላቦራቶሪ ደረጃ ፍተሻ ከሚካሄድባቸው መስፈርቶች መካከል አብዛኛዎቹ የሚከተሉት ናቸው፡-
   - Physical Characterstics
   - Uniformity of Dosage Units
   - Identification
   - Related substances, Dissolution and  Assay
   - Limit test
   - Optical Rotation
   - Microbiological analysis
   - Condom testing
   - Proximate analysis
   - Other tests related to food, Medicine and medical devices
2) ከላይ የተዘረዘሩትን የተለያዩ የጥራት መለኪያ መስፈርቶችን በተፈለገው ጊዜ እና ጥራት  ለማከናወን ባለሙያው እና ሌሎች ሰራተኞች ከመደበኛ የመንግስት የስራ ሠዓት በተጨማሪ ስራዎችን ማከናወን ይጠበቅባቸዋል፡፡

# ክፍል ሶስት

## ከስራው ጋር ቀጥተኛ እና ተያያዥ ተግባራት የሚያከናውኑ የባለስልጣኑ ሰራተኞች፣የስራ ድርሻ እና ኃላፊነት

## 6. ከስራው ጋር ቀጥተኛ እና ተያያዥ ተግባራት የሚያከናውኑ የባለስልጣኑ ሰራተኞች

ለዚሁ አፈጻጸም ሲባል ከስራው ጋር ቀጥተኛ እና ተያያዥ ተግባራት የሚያከናውኑ የባለስልጣኑ ሰራተኞች የሚባሉት፡-

1) በላቦራቶሪ ጥራት ምርመራ ላይ በቀጥታ ተሳትፎ ያደረጉ ባለሙያዎች፤
2) የጥራት ምርመራውን ያስተባበሩ፣ የጥራት ምርመራ ውጤትን ትክክለኛነት የገመገሙ ወይም ያጸደቁ ሰራተኞች እና አመራሮች፤
3) የጥራት ምርመራ ስራውን ትክክለኛነት የማረጋገጥ ተግባራት ላይ ተሳትፎ ያደረጉ ባለሙያዎች፤
4) በጥራት ምርመራው በረዳትነት ተሳትፎ ያደረጉ ባለሙዎች፤
5) በናሙና እና ኬሚካል አቀባበል፤ አሰረጫጨት፣ አያያዝ እና አወጋገድ ላይ ተሳትፎ ያደረጉ ሰራተኞች፤
6) ለጥራት ምርመራው አስፈላጊ በሆኑ የላቦራቶሪ ግብዐት ግዢ እና ግምገማ ላይ ተሳትፎ ያደረጉ ሰረተኞች እና አመራሮች፤
7) በጥራት ምርመራው ወቅት በላቦራቶሪ መሳሪያ ጥገና ላይ ተሳትፎ ያደረጉ ሰራተኞች እና ባለሙያዎች፤
8) ጥራት ምርመራ ውጤትን መመዝገብ፤ ፋይል ማደራጀት እና መሰል ተግባራት ላይ ተሳትፎ ያደረጉ ጸሀፊዎች እና ሰራተኞች፤
9) በላቦራቶሪ ጽዳት ላይ ተሳትፎ ያደረጉ ሰራተኞች ናቸው፡፡
10) የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀፅ 1 አገላለፅ እንደ ተጠበቀ ሆኖ ከጥራት ምርመራው ጋር በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ መንገድ አስተዋጽዖ ማበርከቱ በሚረጋገጥበት
11) ወቅት ማንኛውም የባለስልጣኑ ሰራተኛ በጥራት ምርመራ ስራው ላይ ሊካተት ይችላል፡፡

## 7. የስራ ድርሻ እና ኃላፊነት

### 1) የፋይናንስ እና አቅርቦት ስራ አመራር ዳይሬክቶሬት

የፋይናንስ እና አቅርቦት ስራ አመራር ዳይሬክቶሬት ለጥራት ምርመራው የሚያስፈልጉ ግብዐቶች በሚፈለገው መጠን፤ አይነት እና ወቅት እንዲቀርብ የሚያደርግ ሆኖ ከታች የተዘረዘሩት ኃላፊነቶች ይኖሩታል፡፡

ሀ) በዚህ መመርያ መሰረት የትርፍ ሰዓት ስራዎችን ከማከናወን በፊት በአጋር አካሉ ወይም በፕሮጀክቱ የተያዘ በጀት ስለመኖሩ ማረጋገጥ፤

ለ) በላቦራቶሪው ፍላጎት ለሚቀርቡ የግዢ ትዕዛዛት የጨረታ ሰነድን ማዘጋጀት እና የግዢ ሂደቱን ማቀላጠፍ፤

ሐ) የክፍያ ጥያቄዎች በዚህ የአሰራር መመርያ መሰረት መሆኑን በማረጋገጥ ለተሰራው ስራ ክፍያ መፈጸም፤

መ) ለተለያዩ ወጪዎች ከፕሮጀክቶቹ ወይም አጋር አካሉ ከመደበው ገንዘብ የተቀነሱትን በየጊዜው ለሚመለከተው የላቦራቶሪው ሃላፊ ማሳወቅ እና ከግዢ ጋር በተያያዘ ላቦራቶሪውን ማማከርን እና የተለያዩ መፍትሔዎችን መጠቆም፤

### 2) የንብረት እና ጠቅላላ አገልግሎት ዳይሬክቶሬት

የንብረት እና ጠቅላላ አገልግሎት ዳይሬክቶሬት ከታች የተዘረዘሩት ኃላፊነቶች ይኖሩታል፡፡

ሀ) በላቦራቶሪው ፍላጎት ከፕሮጀክቱ ጥራት ምርመራ ጋር ተያይዞ የሚቀርቡ ማንኛውንም የጠቅላላ ስራዎች ፍላጎት በወቅቱ ማሟላት እና ሂደቱን ማቀላጠፍ፤

ለ) ላቦራቶሪው አጠቃላይ የጥገና፤ የትራንስፖርት ሰርቪስ እና መሰል ተግባራትን በሚፈልግበት ወቅት አስፈላጊውን ፈጣን ምላሽ መስጠት፤

### 3) የዋናው እና የቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች የምግብ፤ መድኃኒት እና የህ/መ/መሳ ጥራት ምርመራ ላቦራቶሪ

የዋናው እና የቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች የምግብ፤ መድሀኒት እና የህ/መ/መሳ ጥራት ምርመራ ላቦራቶሪ ከታች የተዘረዘሩት ኃላፊነቶች ይኖሩታል፡፡

ሀ) በዚህ መመርያ መሰረት የትርፍ ሰዓት ስራዎችን ከማከናወን በፊት በአጋር አካሉ ወይም በፕሮጀክቱ የተያዘ በጀት ስለመኖሩ ማረጋገጥ፤

ለ) በፕሮጀክት መልክ ለሚሰሩ ስራዎች ፕሮፖዛል መቅረጽ፣ መወዳደር

ሐ) ከጥራት ምርመራው ጋር ተያይዞ ጥቅም ላይ ሊውሉ የሚችሉ ማናቸውንም ግብዐቶች መለየት፣ አስፈላጊውን ስፔስፊኬሽን ማዘጋጀት፣ግዢ እንዲፈጸም ትዕዛዝ ማቅረብ እና የግዢ ጨረታ ዶክመንቶችን ቴክኒካል ግምገማ ማከናወን፣

መ) ከጥራት ምርመራ ስራው ጋር ቀጥተኛ ተያያዥነት ያላቸውን ተግባራት ማከናወን ማለትም ጥራት ምርመራ ማከናወን፣ መገምገም፣ ማጽደቅ እና ጥራት ምርመራ ውጤቱን ለሚመለከተው የስራ ክፍል ማቅረብ፣

ሠ) ለጥራት ምርመራው አስፈላጊ የሆኑ ሰነዶችን ማዘጋጀት እና መገምገም፣ የጥራት ምርመራውን ውጤት መሰረት በማድረግ ትንታኔዎችን ማዘጋጀት

ረ) በጥራት ምርመራ ስራው ላይ ተሳትፎ ያደረጉ ሰራተኞች በቅጽ-6 መሰረት ውል እነዲገቡ ማድረግ እና በገቡት ውል መሰረት ሃላፊነታቸውን በአግባቡ ስለመወጣታቸው ክትትል ማድረግ

ሰ) የክፍያ ጥያቄዎችን በዚህ የአሰራር መመርያ መሰረት ማቅረብ፣

## 8. የባለሙያው ወይም የድጋፍ ሰጪ ሰራተኛው ግዴታ

በምርመራ ስራ ላይ የተሰማራ ማንኛውም ባለሙያ ወይም ሰራተኛ

1) የተሰጠውን ስራ በሚፈለገው መጠን፣ጊዜ እና ጥራት የመስራት
2) የሙያውን እና የመስሪያ ቤቱን የአሰራር ደንቦች እና መመሪያዎች የማክበር
3) ከስራ መሪዎች እና ባልደረቦቹ ጋር ተግባበቶ እና ተከባብሮ የመስራት
4) ለዚሁ ስራ የተመደበውን የጊዜ ሰሌዳ በአግባቡ መጠቀም
5) ለስራው የተሰጡትን መሳሪያዎች እና ግብአቶች በጥንቃቄ እና በአግባቡ የመጠቀም፣ ሲበላሹ ወይም እክል ሲገጥማቸው ወዲያዉኑ ለቅርብ አለቃው የማሳወቅ
6) ከቅርብ አለቃውም ሆነ ከስራ መሪዎች የሚሰጠውን ተገቢ ትእዛዝ ተቀብሎ የመተግበር
7) ስራው ላይ ስህተት ሲከሰት ወይም ችግር ሲኖር ወዲያውኑ ለሚመለከተው አካል የማሳወቅ እና እንዲታረም ተገቢውን እርምጃ የመውሰድ
8) የምርመራ ውጤቱን በተገቢው ሁኔታ በግልፅ እና በጥራት የመመዝገብ
9) ናሙናዎችን ሙያው በሚጠይቀው የአሰራር ስርአት መሰረት የመቀበል፣የመለየት፣የመመርመር እና የማስወገድ
10) ስራውን ሲጨርስ ክፍሉንም ሆነ መሳሪያዎቹን ለክፍሉ መደበኛ ስራ ዝግጁ የማድረግ

11) በማንኛውም ጊዜ የላብራቶሪ ምረመራ ስራ ላይ ሲመደብ የመስራት፤ ለመስራት የማይችል ከሆነም ከሶስት የስራ ቀናት አስቀድሞ ለቅርብ አለቃው የማሳወቅ

12) በማናኛውም ጊዜ እና ቦታ የላብራቶሪውን አለም አቀፍ እና ሀገር አቀፍ ደረጃ እና እውቅና ወይም የባለስልጣኑን መልካም ስም እና ደህንነት ከሚጎዱ ማናቸውም ድርጊት እና እንቅስቃሴ የመጠበቅና የማስጠበቅ ግዴታ አለበት፡፡

## ክፍል አራት
## የአከፋፈል ስሌት እና ቀመር

### 9. የጥራት ምርመራ ገቢ እና ወጪ የአጠቃቀም ስሌት

1) ከአጋር አካላት የገንዘብ ድጋፍ ያለው የጥራት ምርመራ በሚከናወንበት ወቅት ቀጥሎ የተዘረዘሩት ቀጥተኛ እና ቀጥተኛ ያልሆኑ ወጪዎች ከባለስልጣኑ ይሸፈናሉ

ሀ) ለጥራት ምርመራው እንደ ግብዐትነት የሚውሉ የተለያዩ ኬሚካሎች፤ ሪኤጀንቶች እና መሳርያዎች ግዢዎች ወጪ፤

ለ) በጥራት ምርመራ ወቅት የሚያጋጥሙትን የመሳርያ ብልሽትን ለማስተካከል እና የመሳርያውን የመጠቀሚያ ጊዜን ለማርዘም እና ለካልብሬሽን የሚውል ወጪ፤

ሐ) የጥራት ምርመራውን ተዓማኒነት ለማረጋገጥ እና አለምአቀፍ እውቅና ለማስቀጠል ያለ ወጪ የላቦራቶሪ ኦዲት፤ ፕሮፌሽንሲ ቴስት እና ሌሎችም የተቀሩት ወጪዎች፤

መ) በጥራት ምርመራው ወቅት የሚከሰቱ የስራ ማስኬጃ እና ሌሎች ወጪዎች በ ቅጽ- 1 በተገለጸው ስሌት መሰረት ከተገኘው የጥራት ምርመራ ገቢ የሚከፈል ይሆናል፡፡

2) አጋር አካሉ ለጥራት ምርመራው የሚስፈልገውን ግብዐቶች ወጪን በሚሸፍንበት ወቅት

ሀ) ለጥራት ምርመራው ስራ የሚያስፈልጉ የግብዐት ግዢ እና የመሳርያ ጥገና ወጪዎች በአጋር አካሉ ወይም በፕሮጀክቱ ባለቤት በሚሸፈንበት ጊዜ ለጥራት ምርመራ አገልግሎቱ ገቢ የተደረገው ገንዘብ በ ቅፅ-2 በተቀመጠው አግባብ የሚፈጸም ይሆናል፡፡

ለ) ከስራው ጋር ቀጥተኛ እና ተያያዥነት ያለው ተግባር ከመደበኛ የመንግስት የስራ ሰዓት ውጪ ለሚያከናውኑ ባለሙያዎች የሙያ እና የኤክስፐርትነት ተግባር እና የጥራት ምርመራው ተዓማኒነትን ለማረጋገጥ በሚደረግ የአለምአቀፍ እውቅና ዙርያ ለተደረገ እና የተለያዩ አጠቃላይ ወጪዎች በባለስልጣኑ የሚሸፈኑ ይሆናል፡፡

3) የጥራት ምርመራው በፕሮጀክት መልክ በሚከናወንበት ወቅት ቀጥሎ የተዘረዘሩት ቀጥተኛ እና

ቀጥተኛ ያልሆኑ ወጪዎች ከፕሮጀክቱ ከተያዘው ገንዘብ የሚሸፈን ሆኖ፡-

ሀ) ፕሮጀክቱን በመቅረጽ፤የጨረታ ዶክመንቶችን በማዘጋጀት እና በመገምገም፤የፕሮጀክቱን ገንዘብ በማስተዳደር ስራ ላይ ተሳትፎ ላደረጉ ሰራተኞች የማትግያ ክፍያ፤

ለ) ከጥራት ምርመራ ስራው ጋር ቀጥተኛ እና ተያያዥነት ያለው ተግባር ከመደበኛ የመንግስት የስራ ሰዓት ውጪ ለሚያከናውኑ ባለሙያዎች የማትግያ ክፍያ፤

ሐ) ለጥራት ምርመራው እንደ ግብዐትነት የሚውሉ የተለያዩ ኬሚካሎች፤ ሪኤጀንቶች እና መሳርያዎች ግዢዎች ወጪ፤

መ) በጥራት ምርመራ ወቅት የሚያጋጥሙትን የመሳርያ ብልሽትን ለማስተካከል እና የመሳርያውን የመጠቀምያ ጊዜን ለማርዘም እና ለካልብሬሽን የሚውል ወጪ፤

ሠ) የጥራት ምርመራው ተዓማኒነትን ለማረጋገጥ፣ የአለምአቀፍ እውቅና ለማስቀጠል፣ የላቦራቶሪ ኦዲት፤ ፕሮፌሽንሲ ቴስት እና ሌሎችም የተቀሩት ወጪዎች፤

ረ) በጥራት ምርመራው ወቅት የሚከሰቱ የስራ ማስኬጃ እና ሌሎች ወጪዎች በ ቅጽ- 1 በተገለጸው ስሌት መሰረት ከተገኘው የጥራት ምርመራ ፕሮጀክት የሚከፈል ይሆናል፡፡

4) ከስራው ጋር ቀጥተኛ እና ተያያዥ ተግባራት ላከናውኑ የባለስልጣኑ ሰራተኞች የክፍያ ቀመር

ሀ) ከመድኃኒት ጥራት ምርመራ ጋር በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ መንገድ ከመንግስት የስራ ሰዓት ውጪ ለሚያከናውኑት የሙያ እና የኤክስፐርትነት ተሳትፎ ተከፋይ ይሆናሉ፡፡

ለ) በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 4(ሀ) የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ ተከፋይ ለሚሆኑ ሠራተኞች የክፍልፋይ ቀመሩ የኬሚካልን ተጋላጭነት፤ የሙያ እና የሀላፊነት ወሰንን፤ በጥራት ምርመራው ላይ የነበራቸውን የስራ ድርሻ እና ደመወዝን ከግምት ውስጥ ያስገባ ሆኖ በአን ቅጽ (3) በተቀመጠው ክፍልፋይ መሰረት ይሆናል፡፡

ሐ) ለእያንዳንዱ ተሳታፊ የሚደርሰው መጠን በምድቡ ውስጥ ያሉ ተሳታፊዎች ቁጥርን ፤ለስራው የተያዘውን መጠን እና እያንዳንዱ ተሳታፊ ተመጣጣኝ ናሙና እና ስራ የሚሰራ መሆኑ ታሳቢ ያደረገ ሆኖ በተራ. ቁ 11.2 ላይ በተቀመጠው የክፍልፋይ መጠን ያገናዘበ

ሆኖ ቀጥሎ በቅጽ-4 በተገለጸው አግባብ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

መ) ማንኛውም ሰራተኛ ተጨማሪ ስራዎችን ከተመደበው ምድብ ውጪ በሚያከናውንበት ወቅት ባከናወነው የስራ ድርሻ መሰረት ክፍያ ይፈጸምለታል፡፡

ሠ) በላቦራቶሪ ውስጥ የሚከናወኑ የጥራት ምርመራ መስፈርቶች ድርሻ ዝርዝር ላቦራቶሪው በሚያዘጋጀው መስፈርት መሰረት የሚዘጋጅ ይሆናል፡፡

## 10. የአከፋፈል ስርዓት

1) የፋይናንስ እና አቅርቦት ስራ አመራር ዳይሬክቶሬት ፡-

ሀ) በላቦራቶሪው ዳይሬክተር የተረጋገጠ ዝርዝር የጥራት ምርመራ ተግባራትና የተሳታፊዎች ዝርዝር ከመሸኛ ደብዳቤ ጋር ሲደርሰው፤

ለ) በባለስልጣኑ በምግብና መድኃኒት ጥራት ምርመራ ም/ዋ/ዳይሬክተር ጥያቄው አግባብ መሆኑ ሲረጋገጥ እና የክፍያ ጥያቄው በዚህ የአሰራር መመርያ መሰረት መሆኑ ሲረጋገጥ አስፈላጊውን ክፍያ ይፈጽማል፡፡

2) በዚህ መመሪያ ላይ የተቀመጠው የአከፋፈል ስሌት በማንኛውም ጊዜ እንደሁኔታው ሊሻሻል ወይም ሊለወጥ ይችላል ፤

3) የተፈቀደ በጀት በባለስልጣኑ ሂሳብ እንደተዘዋወረ ለእያንዳንዱ ሰራተኛ ክፍያው የሚፈፀም ይሆናል፡፡

4) ለባለሙያው ወይም ለሰራተኛው እንዲከፈል የተላለፈው የሂሳብ ስሌት ስህተት ቢገኝበት እንዲታረም እና ክፍያው በተስተካከለው ስሌት መሰረት እንዲፈጸም ይደረጋል፤

5) የምርመራ ስራው ሙሉ በሙሉ ከመጠናቀቁ አስቀድሞ ስራው ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት መቋረጡ በሚመለከተው አካል ሲረጋገጥ በስራው ላይ የተሳተፉ ባለሙያዎች እና ሰራተኞች እንደየስራ ድርሻቸው መጠንን ከግምት ባስገባ ሁኔታ ተሰልቶ ክፍያእንዲፈጸም ይደረጋል፡፡

6) ማናኛውም ክፍያ ከገቢ የሚገኝ የቀረጥ ክፍያዎች እና የተረጋገጡ ሌሎች የመንግስት እዳዎች ተቀናሽ ይደረግበታል፡፡

## ክፍል አምስት
## አስተዳደራዊ እርምጃ እና የቅሬታ አቀራረብ

### 11. ቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ በምርመራ ስራው ላይ የሚሳተፍ ባለሙያ ወይም ሰራተኛ

1) የተሰጠው የጥራት ምርመራ ውጤት በተፈለገው አይነት፣መጠን እና ጥራት አለመከናወኑ በሚመለከተው አካል ሲረጋገጥ እክል ያጋጠመበትን ስራ ሂደት መነሻ

በማድረግ ምርመራው ካለምንም ተጨማሪ ክፍያ እንዲከናወን ይደረጋል

2) ስራው የተከናወነው የመንግስት የስራ ሰአትን በከፊል ወይም ሙሉ በሙሉ በመጠቀም መሆኑ ከተረጋገጠ ክፍያው እንዳይፈጸም ይደረጋል፡፡ ተፈፅሞም ከሆነ ስራው የተከናወነበትን የመንግስት የስራ ሰአት ታሳቢ በማድረግ ገንዘቡ ተመላሽ እንዲሆን ይደረጋል

3) ባለሙያው ወይም ሰራተኛው የሙያ ስነ ምግባር ወይም የመስሪያ ቤቱን የአሰራር መመሪያዎች በተደጋጋሚ ሲጥስ ከተገኘ እንደሁኔታው በጊዜያዊነት ወይም ለዘለቄታው ከምርመራ ስራው ሊታገድ ይችላል

4) የባለስልጣኑን፣የላብራቶሪውን ወይም የላብራቶሪ ባለሙያዎችን ወይም ሰራተኞችን ብቃት ወይም ክህሎት ወይም ተአማኒነት የሚያሳጣ የሀሰት መረጃ በማንኛውም የመገናኛ መንገድ እና ዘዴ ለሶስተኛ ወገን ያስተላለፈ ባለሙያ ወይም ሰራተኛ ከምርመራ ስራው ላይ ለዘለቄታው ይታገዳል

5) የባለስልጣኑን ወይም የምራመራ ስራውን የአሰራር ምስጢር ለሶስተኛ ወገን አሳልፎ ከሰጠ ከምርመራ ስራው ላይ ለዘለቄታው ይታገዳል

### 12. ቅሬታ ስለማቅረብ

1) በዚህ መመሪያ መሰረት የሚቀርቡ ቅሬታዎችን ተመልክቶ ውሳኔ የሚሰጥ የመድኃኒት ጥራት ም/ዋ/ዳይሬክተር፣ የመድኃኒት ጥራት ምርመራ ዳይሬክቶሬት እና የምግብ ጥራት ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር አባል የሆኑበት የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ይቋቋማል፡፡

2) በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ሌሎች የስራ

ክፍሎችም የዚህ ኮሚቴ አባል ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

3) በዚህ መመሪያ መሰረት በምርመራ ስራው ላይ የሚሳተፍ ማንኛውም ባለሙያ ወይም ሰራተኛ በአከፋፈል፣በስር ምደባ ወይም በሌሎች አስተዳደራዊ ውሳኔዎች ላይ ቅሬታ ቢኖረው ፡-

ሀ) ቅሬታውን አሉኝ ከሚላቸውን የሰነድ እና የሰው ምስክሮች ጋር በዝርዝር እና በፁሁፍ በአምስት የስራ ቀናቶች ቅሬታውን በፁሁፍ ለቅሬታ ሰሚው ኮሚቴ ማቅረብ ይችላል፡፡

ለ) ኮሚቴው ቅሬታ በቀረበለት በአምስት የስራ ቀናቶች ውስጥ ቅሬታውን መርምሮ ውሳኔ ይሰጣል፡፡

ሐ) ኮሚቴው ለውሳኔው የሚረዱ ማንኛውንም የፁኁፍ ሰነዶች የሰው ምስክሮች፤የሙያ እና የአሰራር ስርአቶችን በማስረጃነት ሊጠቀም ይችላል፡፡

መ) ኮሚቴው በቀረበለት የሰነድ እና የሰው ምስክር ማስረጃነት ጉዳዩን መመርመር ከጀመረ በኋላ ያለ ኮሚቴው ፈቃድ ተጨማሪ ማስረጃ ወይም የሰው ምስክርነት ለማቅረብ መጠየቅ አይቻልም፡፡

ሠ ) የቀረበው ቅሬታ የሀሰት ማስረጃ ወይም የሰው ምስክርነት ተጠቅሞ ከሆነ ቅሬታውን ለማጣራት የወጡ ወጪዎችን እሰከ ህጋዊ ወለዱ ለመጠየቅ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘውም ጉዳዩን በባለስልጣኑ የዲሲፕሊን ኮሚቴ እንዲታይ ሊመራው ይችላል፡፡

ረ) ኮሚቴው በተሰጠው ውሳኔ ቅር የተሰኘ ቅሬታ አቅራቢ ውሳኔ በተሰጠ በሁለት የስራ ቀናት ውስጥ ቅሬታውን ለዋና ዳይሬክተር ሊያቀርብ ይችላል፡፡

ሰ) በዋና ዳይሬክተሩ የተሰጠ ውሳኔ የመጨረሻው ይሆናል፡፡

## ክፍል ስድስት
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 13. በመመሪያው ያልተካተቱ ጉዳዮች

በባለስልጣኑ የቁጥጥር ሃላፊነት ስር ያሉ እና በዚህ መመሪያ ስር ያልተካተቱ ጉዳዮችን በሚመለከት ባለስልጣኑ እንደአግባቡ እያየ ያስተናግዳል፡፡

### 14. የመተባበር ግዴታ

ባለስልጣኑ ይህንን መመርያ ለማስፈጸም እንዲችል ጉዳዩ የሚመለከተው ማንኛውም ሰው የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

### 15. ተፈጻሚነት የማይኖራቸው ህጎች

1. ከዚህ መመርያ ድንጋጌዎች ጋር የማይጣጣም ማንኛውም ልማዳዊ አሰራሮች በዚህ መመርያ ውስጥ በተካተቱ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖራቸውም፡፡
2. ይህ መመሪያ የፌዴራል መንግስት ሰራተኞች አዋጅ 515/1999 እና ሌሎች የሀገሪቱ ህጎች ደንቦች እና መመሪዎች ደንጋጌዎችን የሚቃረን አይሆንም

### 16. መመሪያው የሚጸናበት ጊዜ

ይህ መመርያ ከመስከረም/2009 ዓም ጀምሮ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

**የሁሉ ደነቀዉ**

**የኢትዮጵያ የምግብ፣ የመድኃኒትና የጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለሥልጣን**

**ዋና ዳይሬክተር**

## ልዩ ልዩ አባሪ ቅጾች

ቅጽ-1

ባለስልጣኑ ለጥራት ምርመራው አጠቃላይ ወጪን በሚሸፍንበት ወቅት የሚከፈልን የላቦራቶሪ ጥራት ምርመራ ገቢ የአጠቃቀም ስሌት ማሳያ

| በጥራት ምርመራ ወቅት በክፍያ መሸፈን ያለባቸው የወጪ አይነቶች | ከአጠቃላይ ለጥራት ምርመራ ከተያዘው የገንዘብ መጠን ለተለየው የወጪ አይነት የሚውል የገንዘብ መጠን በመቶኛ |
|---|---|
| ከስራው ጋር ቀጥተኛ እና ተያያዥነት ያለው ተግባር ከመደበኛ የመንግስት የስራ ሰዓት ውጪ ለሚያከናውኑ ባለሙያዎች የሙያ እና የኤክስፐርትነት ተግባር የሚውል ክፍያ | 50 በመቶ |
| የጥራት ምርመራው ተዓማኒነትን ለማረጋገጥ በሚደረግ የአለምአቀፍ እውቅና ዙርያ ለተደረገ ወጪ | 10 በመቶ |
| ለጥራት ምርመራው እንደ ግብዐትነት የሚውሉ የተለያዩ ኬሚካሎች፣ ርኤጀንቶች እና መሳርያዎች ግዢዎች ወጪ | 25 በመቶ |
| በጥራት ምርመራ ወቅት የሚያጋጥሙትን የመሳርያ ብልሽትን ለማስተካከል እና የመሳርያውን የመጠቀምያ ጊዜን ለማርዘም የሚውል ወጪ | 10 በመቶ |
| በጥራት ምርመራው ወቅት የሚስተዋሉ ሌሎች አጠቃላይ ወጪዎች (ለምሳሌ፣ ውሀ፣ ኤሌክትሪክ እና ሌሎችም) | 5 በመቶ |

ቅጽ-2

አጋር አካሉ ለጥራት ምርመራው አጠቃላይ ወጪን በሚሸፍንበት ወቅት የሚከፈልን የላቦራቶሪ ጥራት ምርመራ ገቢ የአጠቃቀም ስሌት ማሳያ

| በጥራት ምርመራ ወቅት በክፍያ መሸፈን የሚገባው የወጪ አይነት | ከአጠቃላይ ለጥራት ምርመራ ከተያዘው የገንዘብ መጠን ለተለየው የወጪ አይነት የሚውል የገንዘብ መጠን በመቶኛ |
|---|---|
| ከመደበኛ የመንግስት የስራ ሰዓት ውጪ ለሚከናውኑ የጥራት ምርመራ እና ተያያዥ ተግራት ለባለሙያዎች የሙያ እና የኤክስፐርትነት ተግባር እና ለኬሚካል ተጋላጭነት ማካካሻ የሚውል፤ | 75 በመቶ |
| የጥራት ምርመራው ተዓማኒነትን ለማረጋገጥ በሚደረግ የአለምአቀፍ እውቅና ለማስቀጠል ለሚሰሩ ስራዎች፤ | 10 በመቶ |
| በጥራት ምርመራው ወቅት የሚስተዋሉ ሌሎች አጠቃላይ ወጪዎች | 5 በመቶ |
| በጥራት ምርመራ ወቅት የሚያጋጥሙትን የመሳርያ ብልሽትን ለማስተካከል የሚውል ወጪ | 10 በመቶ |

ከስራው ጋር ቀጥተኛ እና ተያያዥ ተግባራት ላከናወኑ የባለስልጣኑ ሰራተኞች የክፍያ ክፍልፋይ ቀመር ማሳያ

| የተሳታፊዎች ምድብ | ከአጠቃላይ መጠን የሚደርሰው ክፍልፋይ (Ratio) |
|---|---|
| የላቦራቶሪ ጥራት ምርመራ ያከናወኑ ባለሙያዎች፤ | 0.26 |
| የጥራት ምርመራውን ያስተባበሩ፤ የውጤቱን ትክክለኛነት የገመገሙ እና ወይም ያጸደቁ ሰራተኛች እና አመራሮች፤ | 0.2 |
| የጥራት ምርመራ ስራውን ከአለም አቀፍ እውቅና አንጻር ጥራቱን የማረጋገጥ ተግባራት ላይ ተሳትፎ ያደረጉ ባለሙያዎች፤ | 0.17 |
| በጥራት ምርመራው በረዳትነት ተሳትፎ ያደረጉ፤ ባለሙያዎች፤ በናሙና አቀባበል፤ አሰረጫጨት እና አያያዝ ላይ ተሳትፎ ያደረጉ ሰራተኞች እና በኬሚካል አያያዝ እና አቀባበል ላይ ተሳትፎ ያደረጉ ባለሙያዎች/ሰራተኞች፤ | 0.11 |
| ለጥራት ምርመራው አስፈላጊ በሆኑ የላቦራቶሪ ግብዐት ግዢ፤ አቅርቦት እና አጠቃላይ ስራ ላይ ተሳትፎ ያደረጉ ሰረተኞች | 0.05 |
| ለጥራት ምርመራው አስፈላጊ በሆኑ የላቦራቶሪ ግብዐት ግዢ እና አጠቃላይ ስራ ላይ ተሳትፎ ያደረጉ አመራሮች | 0.07 |
| በጥራት ምርመራው ወቅት በላቦራቶሪ መሳርያ ጥገና ላይ ተሳትፎ ያደረጉ ባለሙያዎች፤ | 0.04 |
| የጥራት ምርመራ ውጤትን መመዝገብ፤ ፋይል ማደራጀት እና መሰል ተግባራት ላይ ተሳትፎ ያደረጉ ጸሀፊዎች፤ | 0.02 |
| በላቦራቶሪ ግላስዌሮች ጽዳት ላይ ተሳትፎ ያደረጉ ሰራተኞች | 0.04 |
| በላቦራቶሪ ጽዳት ላይ ተሳትፎ ያደረጉ ሰራተኞች | 0.02 |
| የላቦራቶሪ ቢሮ ረዳቶች፤ | 0.02 |

## ሠንጠረዥ 4፡ የተሳታፊዎች ምድብ እና ለእያንዳንዱ ተሳታፊ የሚደርሰው መጠን ማሳያ

| ተ.ቁ | የተሳታፊዎች ምድብ | የክፍፍል ቀመር (R) | በምድቡ ውስጥ ያሉ ተሳታፊዎች ብዛት (N) | የተሳታፊ ዎችን ብዛት ያገናዘበ የክፍፍል ቀመር (N*R) | ለተሳታፊዎች ምድብ የሚኖረው የክፍፍል ቀመር (Y) | ለተሳታፊው ምድብ የሚደርሰው መጠን (Z) | ለእያንዳ ንዱ ተሳታፊ የሚደርሰ ው መጠን |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1. | በላቦራቶሪ ጥራት ምርመራ ላይ በቀጥታ ተሳትፎ ያደረጉ ባለሙያዎች፤ | 0.21 | N | N*R | N*R/ (SUM N*R:N*R) | Y/ለጥራት ምርመራው የተያዘ በጀት | Z/N |
| 2. | የጥራት ምርመራ ውጤትን የገመገሙ እና ወይም ያጸደቁ ሰራተኞች እና አመራሮች፤ | 0.20 | N | N*R | N*R/ (SUM N*R:N*R) | Y/ለጥራት ምርመራው የተያዘ በጀት | Z/N |
| 3. | የጥራት ምርመራውን ጥራት የማረጋገጥ ተግባራት ላይ ተሳትፎ ያደረጉ ባለሙያዎች፤ | 0.19 | N | N*R | N*R/ (SUM N*R:N*R) | Y/ለጥራት ምርመራው የተያዘ በጀት | Z/N |
| 4. | በጥራት ምርመራው በረዳትነት ተሳትፎ ያደረጉ፤ ባለሙያዎች፤ በናሙና አቀባበል፤ አሰረጫጨ እና አያያዝ ላይ ተሳትፎ ያደረጉ ሰራተኞች እና በኬሚካል አያያዝ እና አቀባበል ላይ ተሳትፎ ያደረጉ ባለሙያዎች/ሰራተኞች፤ | 0.10 | N | N*R | N*R/ (SUM N*R:N*R) | Y/ለጥራት ምርመራው የተያዘ በጀት | Z/N |
| 5. | ለጥራት ምርመራው አስፈላጊበሆኑ የላቦራቶሪ ግብዐት ግዢ እና | 0.06 | N | N*R | N*R/ (SUM N*R:N*R) | Y/ለጥራት ምርመራው የተያዘ | Z/N |

| | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | አጠቃላይ ስራ ላይ ተሳትፎ ያደረጉ ሰረተኞች | | | | | በጀት | |
| 6. | ለጥራት ምርመራው አስፈላጊበሆኑ የላቦራቶሪ ግብዐት ግእና አጠቃላይ ስራ ላይ ተሳትፎ ያደረጉ አመራሮች | 0.08 | N | N*R | N*R/ (SUM N*R:N*R) | Y/ለጥራት ምርመራው የተያዘ በጀት | Z/N |
| 7. | በጥራት ምርመራው ወቅት በላቦራቶሪ መሳሪያ ጥገና ላይ ተሳትፎ ያደረጉ ባለሙያዎች፤ | 0.06 | N | N*R | N*R/ (SUM N*R:N*R) | Y/ለጥራት ምርመራው የተያዘ በጀት | Z/N |
| 8. | የጥራት ምርመራ ውጤትን መመዝገብ፤ ፋይል ማደራጀት እና መሰል ተግባራት ላይ ተሳትፎ ያደረጉ ጸሀፊዎች፤ | 0.03 | N | N*R | N*R/ (SUM N*R:N*R) | Y/ለጥራት ምርመራው የተያዘ በጀት | Z/N |
| 9. | በላቦራቶሪ ግላስዌሮች ጽዳት ላይ ተሳትፎ ያደረጉ ሰራተኞች | 0.03 | N | N*R | N*R/ (SUM N*R:N*R) | Y/ለጥራት ምርመራው የተያዘ በጀት | Z/N |
| 10. | በላቦራቶሪ ጽዳት ላይ ተሳትፎ ያደረጉ ሰራተኞች | 0.02 | N | N*R | N*R/ (SUM N*R:N*R) | Y/ለጥራት ምርመራው የተያዘ በጀት | Z/N |
| 11. | የላቦራቶሪ ቢሮ ረዳቶች፤ | 0.02 | N | N*R | N*R/ (SUM N*R:N*R) | Y/ለጥራት ምርመራው የተያዘ በጀት | Z/N |
| 12. | ድምር | 1.00 | የአጠቃላይ ተሳታፊዎች ድምር (SUM N:N) | የተሳታፊዎችን ብዛት ያገናዘበ የክፍፍል ቀመር ድምር (SUM N*R:N*R) | 1.00 | ለጥራት ምርመራው የተያዘ በጀት | |

በፕሮጀክት መልክ ለተቀረጸው የጥራት ምርመራ ስራ ጋር ቀጥተኛ እና ተያያዥ ተግባራት ላከናወኑ የባለስልጣኑ ሰራተኞች የማትግያ ክፍያ ክፍልፋይ ቀመር ማሳያ

| የተሳታፊዎች ምድብ | ከአጠቃላይ መጠን የሚደርሰው ክፍልፋይ (Ratio) |
|---|---|
| ፕሮጀክቱን በመቅረጽ፣ ፕሮፖዛለን በማዘጋጀት ላቦራቶሪው የጥራት ምርመራውን እንዲያሸንፍ ያደረጉ እና የላቦራቶሪ ጥራት ምርመራ ያከናወኑ ባለሙያዎች፣ | 0.26 |
| የጥራት ምርመራውን ያስተባበሩ፣ የውጤቱን ትክክለኛነት የገመገሙ እና ወይም ያጸደቁ ሰራተኛች እና አመራሮች፣ | 0.2 |
| የጥራት ምርመራ ስራውን ከአለም አቀፍ እውቅና አንጻር ጥራቱን የማረጋገጥ ተግባራት ላይ ተሳትፎ ያደረጉ ባለሙያዎች፣ | 0.17 |
| በጥራት ምርመራው በረዳትነት ተሳትፎ ያደረጉ፣ ባለሙያዎች፣ በናሙና አቀባበል፣ አሰረጫጨት እና አያያዝ ላይ ተሳትፎ ያደረጉ ሰራተኞች እና በኬሚካል አያያዝ እና አቀባበል ላይ ተሳትፎ ያደረጉ ባለሙያዎች/ሰራተኞች፣ | 0.11 |
| ለጥራት ምርመራው አስፈላጊ በሆኑ የላቦራቶሪ ግብዐት ግዢ፣ አቅርቦት እና አጠቃላይ ስራ ላይ ተሳትፎ ያደረጉ ሰረተኞች | 0.05 |
| ለጥራት ምርመራው አስፈላጊ በሆኑ የላቦራቶሪ ግብዐት ግዢ እና አጠቃላይ ስራ ላይ ተሳትፎ ያደረጉ አመራሮች | 0.07 |
| በጥራት ምርመራው ወቅት በላቦራቶሪ መሳርያ ጥገና ላይ ተሳትፎ ያደረጉ ባለሙያዎች፣ | 0.04 |
| የጥራት ምርመራ ውጤትን መመዝገብ፣ ፋይል ማደራጀት እና መሰል ተግባራት ላይ ተሳትፎ ያደረጉ ጸሀፊዎች፣ | 0.02 |
| በላቦራቶሪ ግላስዌሮች ጽዳት ላይ ተሳትፎ ያደረጉ ሰራተኞች | 0.04 |
| በላቦራቶሪ ጽዳት ላይ ተሳትፎ ያደረጉ ሰራተኞች | 0.02 |
| የላቦራቶሪ ቢሮ ረዳቶች፣ | 0.02 |

ቅጽ-6

**ቀን፡-------------------------------**

**ውል ሰጪ፡**

**የጥራት ምርመራውን የሚመራው ዳይሬክቶሬት ቡድን ወይም /ቅ/ጽ/ቤት**

**አድራሻ፡**

**ስልክ ቁጥር፡**

**ውል ተቀባይ፡**

**አድራሻ፡** ________________________________________

**ስልክ ቁጥር፡** ________________________________________

**ውል ሰጪ እየተባለ በሚጠራው የጥራት ምርመራውን የሚመራው ዳይሬክቶሬት ቡድን ወይም /ቅ/ጽቤት**

**እና ውል ተቀባይ እየተባለ በሚጠራው ________________________________ መካከል**

**የሚከተለው የውል ስምምነት ተፈፅሟዋል ፡፡**

**<u>አንቀፅ አንድ</u>**

**<u>የውሉ አላማ</u>**

**ውል ተቀባይ የተረከባቸውን ከጥራት ምርመራው ጋር ግንኙነት ያላቸውን የስራ ዝርዝሮች በውል ሰጪው የኳሊቲ ማንዋል፤ የአሰራር ፕሮሲጀሮች፤ በአለም አቀፍ እውቅና ስታንዳርድ፤ በመልካም የላቦራቶሪ ስርዓት እና የጊዜ ገደብ መሰረት ስራዎችን ለውል ሰጪው እንዲያስረክብ ለማድረግ የተፈፀመ ነው፡፡**

**<u>አንቀፅ ሁለት</u>**

**<u>የውል ሰጪ ግዴታዎች</u>**

1. **ውል ሰጪ ስራዎችን ቆጥሮ ያስረክባል፤ የስራዎችን አፈጻጸም በየጊዜው ይገመግማል፤ ስራዎች በተገቢው መልኩ፤ በተፈለገው ጥራት እና በዜጎች ቻርተር ላይ በተቀመጠው የጊዜ ገደብ መሰረት መጠናቀቃቸውን በማረጋገጥ በቅጽ** 4 **መሰረት ክፍያን ይፈጽማል፡፡**

## አንቀፅ ሦስት
## የውል ተቀባይ ግዴታዎች

2. ውል ተቀባይ ከጥራት ምርመራው ጋር ግንኙነት ያላቸውን የስራ ዝርዝሮች ተገቢውን ጥራት ባሟላ መልኩ አከናውኖ ለውል ሰጪ በተቀመጠለት የጊዜ ገደብ ውስጥ የሚያስረክብ ሆኖ የመጨረሻው ማጠናቀቅያ ጊዜ ከሁለት ወር አይበልጥም፡፡

## አንቀፅ አራት
## የክፍያ አፈፃፀም

3. ይህ ውል በተዋዋይ ወገኖች እንደተፈረመና ስራው በትክክል ተሰርቶ ሲያልቅ ውል ሰጪ ክፍያውን ይፈፀማል፡፡

## አንቀፅ አምስት
## አፈጻጸም

4. ይህ ውል በተዋዋይ ወገኖች መካካል ከተፈረመበት ቀን ጀምሮ በሕግ ፊት የፀና ይሆናል፡፡ ተዋዋይ ወገኞች በውል መሰረት ያለባቸውን ግዴታዎች ፈፅመው ባይገኙ በውሉ አለመፈፀም ጉዳት ለደረሰበት ወገን የውሉን ጠቅላላ ዋጋ 30% በፍ/ሕ/ቁ 1889 እና 1986 መሰረት ካሣ እንደሚከፍሉ ተዋዋዩ ተሰማምተዋል፡፡

| ውል ሰጪ | ውል ተቀባይ |
|---|---|
| ______________________ | ______________________ |
| ፊርማ | ፊርማ |
| ______________________ | ______________________ |

**እማኞች**

እኛም ውል ሰጪ እና ውል ተቀባይ ሲፈራረሙ አይተናል፡፡ ይህንንም እንደሚከተለው በፊርማችን እናረጋግጣለን፡፡

| | ስም | ፊርማ | ቀን |
|---|---|---|---|
| 1. | ____________ | ____________ | ____________ |
| 2. | ____________ | ____________ | ____________ |
| 3. | ____________ | ____________ | ____________ |